# የወደቀው የዘር ፖለቲካ ሲያብብ

## በዳላስ ቴክሳስ

ባለፈ ሰሞን ትልቅ ዜና በሁሉም የኢትዮጵያ ሚዲያወች ስለ ዶክተር ነጋሶና አቶ ስዬ አብርሐ አዲስ ዜና አስነብበውናል። በእውነትም አስደሳቹ ዜና አዲስ ባይሆንም አንድ ሌላ ድልን የኢትዮጵያ ብሔርተኝነት አስመዘገበ ማለት ነው። ውብ ዜና ነው። ከውበቱ ላይ ውበት የጨመረለት የዶክተር ነጋሶ ያቀረቡት ሐሳብ ነበር። እኒህን ሰው ማንም ኢትዮጵያዊ እንደሚያውቀው፤ በ፲፱፹፫ ዓ.ም በወያኔ ኢሕአዴግ እጅ ስትገባ በተቋቋመው "የሽግግር መንግስት" ይሉታል ባለስልጣን ሆነው የተሾሙ ሰው ነበሩ። አዎ፤ የኤርትራን አገርነት አስገኘጥሎ ህጋዊ ልባስ በሰጠው ሬፈረንደምም ጊዜ መልካም ተባባሪ እንደነበሩ ተናግረዋል። ከሁሉም በላይ ባገራችን ፖለቲከኞች ባልተለመደ አንደበት "ተሳስቻለሁ" ያሉም ሰው በመሆናቸው ያያሌ ዜጎችን ቀልብ የሳቡ ናቸው። "ተሳሳትሁ" ያሏቸውንም በዝርዝር አቅርበዋል። እኛም መልካም ጅማሮአልን።

ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ እንዳሉት ከልጅነት ጥርስ የነቀሉበት ጎጣዊ፤ ክልልተኛና ዘረኛ አስተሳሰብን አሁን ላይ ቆመው ሲያስቡት እንዳዘኑበት ተናግረዋል። በተለየም "ሕገመንግስት" ተብየውን የወያኔ/ኢሕአዴግ ቧልት በጣም አወገዙ በመግለጫቸውም ይቅርታ ጠየቁ።

ለዶክተሩ እዚህ አስተሳሰብ ላይ እንዲደርሱ ያድረጋቸው፣ ያ ከወያኔወችና ከአኦነግ ጋር ሆነው የተለያየ ስም የለገሱት በቋንቋ፣ በሀይማኖቱ ነጣጥለው የመቶ አመት ታሪ ነዉ ያለህ ቀሪው ተረት፣ ተረት ነው በማለት general Petro Bodolio አንዲ አበባ በገባ በ ፩፪ኛው ቀን አገሪቱን አጥፍቶ በቋንቋ ሸብሸኖ ቢያጠፋትም የፋሽስቶች ምኞት ለአምስት አመታት ብቻ ነበር እውን የሆነው። አገራችን ያኔም በሰማእታት ደምና አጥንት ያነን የተሸረበባትን የጥፋት ዘመቻ አቸንፋ እስከ አለንበት ቀጥላለች። ወያኔ፣ ኦነግና ሌሎች ምናምኖች ስልጣን በጨበጡ ማግስት ከቦዶሊዮ ተምረው ከሱ በላቀ የከፋፍለህ አባልተው ሊያጠፋት ቢሞክሩ ሳይሆንላቸው ቀርቷል። በበደኖ፣ በአርባ ጉጉ፣ ያሳዩትን አሳፋሪ ድርጊት እነሱ ወገን ከወገኑ ቂምና በቀል እንዲቋጥር ብለው በዘየዱት የቪዲዮ ድራማ አሳይተዋል። የተቻላቸውን ሁሉ አድርገው ከፋፍለውና አጋጭተው የበደሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሉን ተሸክሙና ታግሶ ያሳየው ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ከልባቸው የማይጠፋ ለአስተሳሰብ ለውጣቸውም ምክንያት ሆነልኝ ነበር ያሉት። በሳቸው አንደበትም አሁንም እንደቀድሞ አስተሳሰባቸው እስካሁን የሚያስቡትን ዘረኞች ምሁራዊ በሆነ ቋንቋ ወቅሰዋል። “ስለአንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሚያስቡ፣ ስለአንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሚቆረቆሩ፣ ስለአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ብለው ኢትዮጵያዊነትን የሚታገሉ ዋናው ስህተታቸው ያለው ከእንቁላሏ እንዳልወጣች ጫጩት መሆናቸው ነው ይላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይ፣ ቅንና እሩህሩህ መሆኑን አልሸሸጉም። ታዲያ ያነን የቆዩበትን የዘር ፖለቲካና ክልልተኛነት መልሰው ላለማየት ነው ወደ አንድነት ፓርቲ የተቀላቀሉት እንዳባባላቸው ነው። እኛም እሰየው እንላለን።

አቶ ስዩ አንርሐም የዶክተር ነጋሶን ያክል ባይሉም፣ የዘር ፖለቲካን ዳግም ላለማየት መወሰናቸው በጣም ያስመሰግናል። ይበርቱ እያልን ሆኖም ልክ እንደባልንጀራቸው ሁሉ የሰሩትንና ለምንስ ያደጉበትን (ጥርሳቸውን የነቀሉበትን) አስተሳሰብ እንደተውት፣

EthioLion.Com

ብሎም እንደዶክተሩ ነበር የሚሉትን ስህተቶች በተለይም ከ፲፱፻፱፪ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወዲህ ደጋግመው የሚሉትን አገራችን የባሕር በር ማሳጣት በሳቸውና በመሰል ጓዶቻቸው ፊታውራሪነት ኤርትራ ለተባለች እነሱ አገር ብለው ስለፈጠሯት ኢትዮጵያዊት ክፍለግዛት አሳልፈው መስጠታቸው ያስቀረቀራቸው መሆኑን ሕዝብም ሆነ ሌላው የፖለቲካ ሰው በስማበለው ያውቃል። በእርግጥም የሕወሐት ለሁለት መከፈል አንዱ እንደሆነ ደጋግመው ከመለስ አንጻር የቆሙት እንደተናገሩም እናስታውሳለን። ያብሻ አይደለም ብዙ ዜጎች መጀመሪያ በትግራይ ውስጥ ኋላም አገሪቱን ከተቆጣጠሩ በኋላ ተበድለዋል፣ ታስረዋል፣ ተገለዋል፣ መዳረሻቸውም የጠፋውን ቤት ይቁጠራቸው። ለዚያ ሁሉ የበኩላቸው አስተዋጾኦ ለመኖሩ አጠራጣሪ አይደለም። ከሆነ ላይቀር ይህን በጎጥ፣ በቋንቋ፣ በክልል የተከፋፈለ ትውልድ ሊማር የሚችለው፣ ይህችንም አገር እየናጣት ካለው ዘረኝነት ማውጣትም የሚቻለው የራስን ገመና (ያደባባይ ሚስጥር ነው) አውጥቶ ማሳየቱ ትውልዱን ያድነዋል። በዚህ በኩል አቶ ስዬ በዘር ዳግም መደራጀትን የናቁትን ያክል ክፋትና አጥፊነቱን ባንደበታቸው ማውጣቱ ጠቃሚም  አስፈላጊም ነው እንላለን።

በእርግጥም የዚህ ዘረኝነት ስራት ጎጅነቱን አይተው አይሆንም የሚሉ ወገኖቻችንን ያበባ ጉንጉን ይዘን ልንቀበል ይገባል። በዶክተሩ አባባል አንጻር ስንመለከት ክልጅነት እስከአዛውንትነት ያደረሳቸው በኦሮሞ ጥያቄ ዙሪያ አይቸው ቀይቻለሁ ያሉት አመለካከት ሕዝባችንን በተለየም ሰፊውንና ለዘመናት የዚህችን አገር ዳር ድንበር አጥንቱን ከስክሶ ደሙን አፍሶ ሲያስጠብቃት የኖረውን የቆዩበት የፖለቲካ መስመር ክፍል ክብርና ዝና ያጎደፈ ለሰሜን ተግንጣዮች ማስፈራሪ ሆኖ የቀየ እስካሁንም ለውያኔም ሆነ ለሻብያ ባንድ ወይም በሌላ መሳሪ መሆኑ የሚያሳዝን ነው። ትናንት ሳይቀር በባድሜ ለተደረገው ውጊያም ሆነ በናቅፋና፣ በምጽዋና በመላው ኤርትራና

ትግራይ ያገር አንድነትን ለማስጠበቅ በተደረገው ተጋድሎ በኦርምኛ ተናጋሪ ሕዝባችን የፈሰሰው ደም ዛሬም ይጣራል። ያነን ሰምቶ ወደጤነኛ መስመር መመለስ ለዘመናት ለተዘመረለት፣ አያሌ ሰማእታት ለወደቁለት የዴሞክራሲ የእኩልነት የሰበአዊ መብት ላዴ ለመጨረሻ ክብር መጎናጸፍ ሲባል ለተድረገውና እየተካሄደ ላለው ተጋድሎ ትልቅ እመርታ ነው።

ይህ “በሕዝባዊ ወያኔ ትግራይ” እና በሻቢያ፣ ኦነግ ተቦክቶና ተሰልቆ በሕዝብ ጉሮሮ የተሰካ ፋሽስታዊ አስተዳደር ፩፱፱፯ በምርጫ ሳጥን ባፍ ጢሙ ተደፍቷል። ዘረኝነትና ዘረኞች አፍረውበታል። ወያኔወችና ሌሎች ዘረኞች ከምርጫው ማግስት እንዳሉት የወያኔን የዘር፣ የጎጥ፣ የመንደር ፖለቲካ የሚቃወሙት ነፍጠኞች ማለትም (አማርአኛ ተናጋሪው) ብቻ አልነበረም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ፣ በአደጉት አገሮች እንኳን ያልታየ የመራጭ ቁጥር 80% እንደነበር በጊዜው ገዥው ወያኔ ሳይቀር አምኗል። ከደቡብ እስከሰሜን፣ ከምእራብ እስከምስራቅ በድምጽ (secret ballot) አጋጣሚውን ተጠቅሞ ሕዝቡ የሚፈልገውን አሳይቷል (መርጧል)። ዛሬ አክ እንትፍ ተብሎ የተተፋውን የሞሶሎኒን፣ የሂትለርን፣ የሞቡቱን፣ የኤዲያሚንንና የመንግስቱ ሐ/ማሪያምን ስርአት ለማስቀጠል ይሁነኝ ቢሉም ከማህላቸው የሚያፌተልከው በዝቷል። የጊዜ ጉዳይ እንጅ ይህ ዘረኛ መንግስት አጓጉል መውደቁ አይቀሬ ነው።

የዘር ፖለቲካ አስተሳሰብ፣ ጎጠኝነት፣ ክልልተኝነት ከማንምና ከምንም ጊዜ በላይ ባገራችን የተጠላ መሆኑን በገሐድ አይተናል። ፊደል የቆጠረ ቀርቶ እድሉን ያላገኘውና ካካባቢው አልፎ የሌላውን ኑሮ ሁናቴ ያላወቀው ወገናችን ጸያፍነቱን የተረዳበት ጊዜላይ ደርሰናል።

EthioLion.Com

ወያኔ ያመጣብን ስርአት ባገራችን ከመቸውም ጊዜ የተጠላበትና የተናቀበት ጊዜ ነው። ባንጻሩ እዚህ በዲአይስፖራ ያሉ በድሀው ወገናችን ላይ የሚደርሰውን በደል ከጉዳይ ያላሉ፣ ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ማንነታቸውን ትተውት ለሚያለፉት መሬት ሲሉ አዋርደው የወያኔን አላማ ሲያስፈጽሙ ሞልተው ተርፈዋል። እነዚህ ሰወች ሰርተው ሀብት ሊያገኙበት ተምረው ሊያውቁ ሊመራመሩበት በሚችሉበት አገር እየኖሩ ለወያኔ የፖለቲካ ደላላ በመሆን ከፍ ዝቅ ሲሉ ይውላሉ።

የዲያስፖራ አዲስ ምልምሎች

ከላይ ባሳየነው ያገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ወያኔና አጋር የአንቀጽ ፴፱ አራማጆችና ደጋፊወች ባሰቡት ባለሙት መንገድ ሳይሆን አገሪቱናሕዝቧ የተጫነበትን የመገንጠል ትችላለህ የዘር የቋንቋ ክፍፍልን ጥሎ አንድነቱን አስጠብቆ እየኖረ ነው። ወያኔና መሰል ገንጣይ ድርጅቶች ዛሬም ከ፳፱ አመት አገዛዛቸው በኋላ የክልል ነጻአውጭ ነን ማለታቸውን እንደቀጠሉበት ነው። ከቄሱ ዲያቆኑ እንዲሉ ትግራይን እናስገነጥላለን ብለው ጫካ ገብተው ከታገሉት በላቀ መሬትና ቤት አገኛለሁ ብሎ የሚመላለሰው የዲይአስፖራ አድርባዩ የበለጠ አስቸጋሪ ሆኗል። አንድ ወዳጀ የዳላስን የኮሚውኒቲ ራዴዮ አዳምጦ ሲ ጨርስ ደወለልኝና ግራሞቱን ደጋግሞ ሲገልጽ እኔ ማዳመጥ ቀርቶ እሁድ ቀን ሬዲዮም ስለማልከፍት ግራ ገባኝ። ያዳመጥሁ መስሎት ቢደጋግምም ከኔ መልስ በማጣቱ እሱም ገርሞት እንማለት እንዴት ነው ሁሉ ወያኔ ሆነ ማለት ነው ዘንድሮ በማለት እርሱን ሲጠይቅ አደናግጦን። ወያኔን እዚህ ምናመጣው በማለት ምላሽን ሰጠሁ። ወዳጀ አለማዳመጤን ገባውና አይ ይኸው ሁለተኛ ሳምንቱ ነው አንድ የአማራ የልማት ማህበር ነኝ የሚል ግሩፕ ማስታወቂያ በመደጋገም አወጣ። ከሁሉም ገራሚው በዚህ ባለንበት ነጻ አገር በሰላም ተሰርቶ

EthioLion.Com

በሚገባበት መነገድ ቢፈልግ ሰው ገንዘብና እውቀቱ ካለው ከልካይ በሌለበት እየኖርን እነዚህ አገርቤት መሬት ይሰጣችኋል እዚህ በላማት ማህበሩ ተሰባሰቡ የሚል ፕሮፖጋንዳ በማሰራጨት ላይ ናቸው። ወያኔና የወያኔ ፖለቲካ ባገር መተፋቱ እንዳለ ሆኖ ጥቅም በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ስርአቱ አስመርሮት በሰው አገር የሚኖረውን ይህን ታገኛለህ ከኛ ጋር ተሰለፍ በሚል እራሳቸውን ለጥቅም ሸጠው ከዘረኛው ስርአት ጋር የተሰለፉ ወዶ ገቦች ሌላውንም ለመሳብ ያደረጉት ጥረት በዳላስ ነዋሪ ዜጋ ተጋልጧል።

ይህ አሳፋሪ ተግባር በዚህ በዳላስ ብቻ የተሞከረ እንዳልሆነ እናውቃለን። መጭውን ምርጫ ተብየው ወያኔ በሰላምና ምንም ተቃውሞ በሌለው ሁኔታ የራሱን ስርአት ማስቀጠል ይፈልጋል። የውስጡን በሐይል የውጩን መሬት አገኛ ባይ ስብእናውን የሚሸጠውን አይነት ሰባስቦና አሰልፎ፣ አለያም የክፍፍል ፊታውራሪ ያሰልፋቸዋ። ወያኔ እንዲህ አይነቶች እንዳሉ ያውቃል በምልመላው አይቸገርም ጥሩ ልምድ አካብቷል የአድርባይ ለከስካሶችን ስብእና በገንዘብ ወይም በስልጣን መግዛት እንደሚችል ደጋግሞ አይቶታል። በተለይ ዛሬ በውጭ ለመስራት ላሰበው መሬትና ቤት መስጠቱን ተያይዞታል አገር እያመላለሰ በየመሸታው ማዝናናቱን ተያይዞታል። ለዚ የሰለባ ውጤት ከሆኑትና ዛሬ ኮሚውኒቲያችንን ከሚያተራምሱት በዚህ በዳላስ ካየነው አንድ እናካፍላችሁ።

እዚህ ዳላስ አንድ ግለሰብ በደርግ ጊዜ መጀመሪያ ካድሬ ኋላ ለመንግስቱ ሐ/ማሪያም በእድገት የፕሮቶኮል ሹም ሆኖ ያገለለገ አለ። እንደሰማነውና እንደሚታወቀው በዚያን ዘመን የካድሬ ስራና ተግባር ምን እንደነበር መጥቀስ አያስፈልግም። ሆኖም መቸም ቢሆን አንዳንድ ሰወች እድሜም ሆነ እውቀጥ

EthioLion.Com

ከነበሩበት ላይ ቢጨምሩም የባህርይ ለውጥ አይታይም አበው “ተፈጥሮን ተመክሮ አያድነውም” ይላሉ። የአእምሮ ሐኪሞች anti social ይሏቸዋል ይህ ሰው የትኛው እንደሁ ባናውቅም፣ በእርግጥም እሱን መሰል ግለሰቦች ከአንዱ በደላቸው ሳይነጹ ወደሌላ የተላለፉ ባገራችን ሞልተው ተርፈዋል ባይሆን ኖሮ ይህ ያናሳ ጠባብ ብሄርተኛ ማንግስ ብዙ ባልዘለቀ። ግለሰቡ አሁንም ለጊዜው ስሙን መያዝ እንፈልጋለን ምናልባት መታገሻውን ከሰጠው። እዚህ ዳላስ በቤተክርስቲያን፣ በኮሚውኒቲና መሰል ሕዝብ በሰራቸው ስብስቦች ሁሉ በመገኘት ችግር ይቀፈቅፈል። አልፎ ተርፎ አገር በመሄድ አባ ጳውሎስን ተባርኮ ከተመለሰና ወያኔም ያውቅበታል መሬትና ቤት ከታደለ ወዲህ የዚህ ስራት ዋና አራጊ ፈጣሪ በመሆን ቤተክርስቲያናችንን ለጳውሎስ ኮሚውኒቲ ማህበሩን ለወያኔ ካድሬወች ለመስጠት አይተን የማናውቀው በደል፣ ትርምስ ፈጥሯል። ከወያኔ ጋር ሆነው ከታገሉት በላይ የወያኔ ተከላካይና ደጋፊ ነው። ታማኝነቱን ለማስመስከር ከታዘዘው በላይ ይሰራል (ያምሳል)። ወያኔ መሰሪ እንደመሆኑ መጠን እንዲህ አይነቶችን መጋዦች ሰባስቦ በትእዛዝ ያባክናቸዋል ያሰራቸዋል። እንዚህም በደስታ የጫናሉ ይጋለባሉ። ሆዳምና እበላ ባይ ባያገኝ ኖሮ ፳፱ አመት ቀርቶ አንድ ሳምንት ባልቆየ። ከነ አቶ ክፍሌ ወዳጆ ጀምሮ (ነፍሳቸውን ይማርና) እንድርያስ እሸቴ፣ ዳዊት ዮሐንስ፣ ካሱ ኤላላ፣ ገነት ዘውዴ፣ ታምራት ላይኔ ወዘተ እና እስካሁኖቹ አገልጋዮቹ ድረስ ከወርቁ የተፈጠሩ አይደሉም በጥቅምና በፍርፋሪ ስልጣን የተጠጉ በመሆናቸው ለአላፊ ነገር ተለውጠው ይህንም አናሳ የዘረኛ መንግስት እድሜ እዚህ አድረሰዋል። መለስና የወያኔ አመራሮች ዛሬ የትግራይን ሕዝብ በስም እየተጠቀሙ በተግባር አገልጋዮችን ከዚህም ከዚያም ቋንቋ ተናጋሪ ለስራ አሰማርተዋል። ወያኔ ስንል ያንድን ከአንድ ክልል የመጣ እንዳይደለ ሊታወቅ ይገባል ባብዛኛው እበላ ባይ አድርባይ ባንዳ የተሰባሰበበት ጥርቃሞ

EthioLion.Com

ነው። የጉራጌ ልማት፣ የኦሮሞ፣ የአማራ ልማት ድርጅት ወዘተ በሚል ትቂት አድርባዮች የሕዝብ ውክልና ሳይኖራቸው የሚነግዱበት መሰባሰቢይ ሆኗል።

ካለፉት ተከታታይ ሁለት ሳምንታት በዚህ በዳላስ ከተማ በ አ.ል.ማ (ያማራ ልማት ማህበር) ተሰባሰብን የሚሉ ግለሰቦት ማስታወቂያ በማውጣት በስደት አገር ለሚኖረው ወገናችን ኑ ተሰባሰቡ የሚል የቅስቀሳ ጥሪ አስተላልፈዋል። ማሕበሩን መስርተናል ያሉት ግለሰቦች በኮሚውኒቲአችን ይታወቃሉ። ምናልባት አንድ ወይም ትቂቶች ባለማወቅ ተደልለው የተደባለቁና መሰሪ አድርባዮች ስማቸውን መጠቀሚያ ያደረጉም ይመስለናል። ሆኖም ግን ይህ ተመሰረተ የተባለው ስብስብ አገር ውስጥ ልማት እንደሚካሄድና በዚያ ተሳታፊ እንድንሆን ይቀሰቅሳል። አላማና ተግባሩ የአንድን ክልል ሰወች ማሰባሰብ እንደሆነም ተገልጿል። ነገርን ነገር ያነሳዋልና አንድ ወዳጅ ሲያጫውተን አገርቤት ሦስት ልጆቹን ይዞ ይሄዳል ልጆቹን ይዞ ወደዘመድ ቤት ሲሄድ ባጋጣሚ አንደኛው ልጁ ከመንገድ ዳር የወደቀ ትንሽ ልጅ ያያል ታዲያ አባቱ አባክህ አቁም መኪናውን ይህን ትንሽ ልጅ ሞቶ ይሁን ወይም ተጎድቶ እንደሆን ማየት እፈልጋለሁ ብሎ ከመኪና ወርደው ሲመለከቱ ያልጅ ተጠቅሎ ተኝቷል እንጅ የሆነው ነገር የለም። እነዚህ አገር ጎብኝወች ውስጥ ታላቁ ልጅ እንባውን ማቆም አልቻለም። በእርግጥም የሚያሳዝን ትረኢት ነበር ይህ በረንዳ አዳሪ ልጅ በረንዳም ክልክል በመሆኑ መኝታውን ሰው ከማይደርስበት ራቅ ብሎ ከመንገድ ዳር አድርጓል። ኢትዮጵያ ማለት ዛሬ እንደሚሰራው ሕንጻ ያማረች የደመቀች ሳትሆን በውስጧ በሚሊዮኖች ከናትና አባት የተለያዩ ሕጻናትን በየመንገዱ እቤት አርጋ የምታስተናግድ፤ ዜጎች በበሽታና በድህነት የሚንገላቱባት የምድር ሴኦል እንድትሆን በዘረኖችና በአለም አቀፍ ተባባሪወቻቸው የተፈረደባት አገር ናት። “ከእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ” እንዲሉ በመራብ አገሮች መልካም ኑሮ የጀመረ በቱሪስትነት ተመላልሶ የሚደሰትባት ከፊሉ

መሬት ለመመራት ሲል ያየውን አላየሁም ብሎ አገር አደገ ገበያው ጠገበ ብሎ የሚቀጥፍባት አገራችን ናት።

በሰሞኑ እዚህ በስደት በስደት አገራችን ዳላስ የጠላነው ዘረኝነትና የዘር ፖለቲካ ተከትሎን ያማራ ልማት በመንግስት የተደገፈ ማህበር በወያኔ መልካም ፈቃድ አደራጅተናልና ኑተቀላቀሉን እየተባል ነው። ሀፍረተቢሶችና ምናልባትም አንዳንድ የዋሀን በሰላም ተደጋግፈን በኖርንበት የሰው አገር ይህ ዘረኝነትና የዘር ማህበር ማቆቋም ምን ያክል ሊጎዳን እንደሚችል። ማለት አንደአንድ ኮሚውኒቲ ማለት ነው አላወቁም ወይም አልተገነዘቡም። አወ ትቂቶች አውቀውና ተነገንዝበው የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን አውቀናል። የዳላስ ኢትዮጵያውያን ባንድ የኖርን፣ በሐዘን በደስታ የተባበርን አሁንም ያ ትብብር የቀጠለ በመሆኑ ይህን የኑ ተደራጁ ያውም በዘር ተሰባሰቡ የሚለውን ቅስቀሳ ልንቃወም ልናወግዝ ይገባል። አንድነታችን በምንኖርባቸው የዳላስ ቀበሌወች እና አስተዳደሮች የተመሰገነ። የምንታወቀው በሰላማዊነት፣ በሰራተኛነት፣ ለምንኖርባቸው መንደሮች አስተዋጸኦ በማድረግ በጋርላንድ፣ በሪቻርድሰን፣ በፕሌኖ ሲቲወች ለመከበር የበቃነው በአንድነት በትብብር በመደጋገፍ መኖራችን ነው። የዘር የክልል የቋንቋ አስተሳሰብ ያንን መልካም ስምና ተከባሪነት አጥፍቶ፤ የእርስ በርስ መናናቅ ብሎም ገመና ወደውጭ ዘልቆ እንድንናቅ ያደርጋል። ለልጆቻችንም ትርፉ የማያውቁትን ማስተማር ይሆናል። ዛሬ ቤተክርስቲያን መሰባሰቢያችን ፍርድ ቤት ቀርቧል። ዳኞች ይህ ክስ አይገባም ብለው ሲመልሱ ደግሞ እልህ በተሞላበት ይግባኝ መባሉ ለኛም ሆነ ለልጆቻችን መልካም አይደለም እንላለን። ያንን የገባንበትን የፍርድቤት ቀጠሮና ክስ ሳንዘጋ ይህ በዘር ተሰባሰቡ፣ ያውም በተመሳሳይ ግለሰቦች መባሉ በጣም ያሳዝነናል።



EthioLion.com

ይህ መቆም አለበት። ብዙው ዜጋ አገሩን ጥሎ ለስደት የተዳረገው የሰው አገር ናፍቶ ወይም ወዶ አይደለም። ባገራችን የተንሰራፋውን ዘረኝነት፣ የመብት መገፋት፣ የነጻነት ማጣት፣ በሰላም ሰርቶ መግባት አለመቻሉ ነው። በገንዘብ ተገዝተው ያንን የተጠላ አስተሳሰብ ይዘውብን የመጡ ቅጥረኞች ሊያቆሙ ይገባል ሊመከሩ የገባል። በአለም ተዘርቶ አገር ወገኑን ትቶ በሰው አገር በሰው ባሕል በባእድ መሬት የሚኖር ዜጋ ይህ ድርጊት ያሳዝነዋል አቁሙ እንላለን። ዳግም ከተቀጠለበት መጋለጽ ይከተላል። በክፉ ቅን አይዞህ ባይም እንደሚጠፋ እወቁ እንላለን።

ለክፉ አሳቢ ወገኖች ልብ ይስጥ

ጉዳዩ ያሳሰባቸው በዳላስ የሚኖሩ በግል አነሳሽነት የተሰባሰቡ ያወጡት ጥሪ ነው።

EthioLion.Com